Prince William County
PUBLIC SCHOOLS
*Providing A World-Class Education*

ላታንያ ዲ. ማክዴድ Ed.D.
*የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ*

ውድ ወላጅ/አሳዳጊ:

እንኳን ከ149 ቋንቋዎች በላይ ከሚነገሩበት ብዝሃነት ያለበት የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ወደ ፕሪንስ ዊልያም ካውንቲ ፓብሊክ ስኩል(PWCS) በደህና መጡ። የቤተሰብ እና የማህበረሰብ መስተጋብር የአራት አመት ስልታዊ እቅዳችን ቁልፍ የሆነ መሰጠታችን ነው እና በልጅዎ ትምህርት እና የወደፊት ህይወት ላይ አዎንታዊ የሆነ ልዩነት ለማምጣት በጋራ ለመስራት ወሳኝ ነው። በትምህርት ላይ የእርስዎ አጋር እንደመሆናችን፣ በማንኛውም የትርጉም እና ማስተርጎም አገልግሎት እርስዎን ለማገዝ ዝግጁ ነን።

ሁሉም የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች በእንግሊዘኛ ናቸው፣ ነገር ግን ወሳኝ ዶክመንቶች እና አስፈላጊ ንግግሮች በማህበረሰባችን በጣም ተጠያቂ ወደሆኑ ቋንቋዎች ይተረጎማሉ። በተጨማሪም PWCS ብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች አስፈላጊ መረጃ ያላቸውን ዶክመንቶች እንዲረዱ ለማገዝ ፕሮፌሽናል አስተርጓሚዎች እና ተርጓሚዎችን ያቀርባል። ይህም የተማሪዎችን እና የወላጆችን መብቶች፣ ሃላፊነቶች፣ የሚጠበቁ ነገሮች እና ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ያካትታል።

አስተርጓሚዎች በወላጅ/አስተማሪ ኮንፍረንሶች ላይ የትርጉም አገልግሎትም በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ። ይህም ተማሪዎችን በሚመለከት ሲሆን ወላጆች ምንም ወጪ አይኖርባቸውም።

**ልዩ እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ ከእነዚህ መሃል የትኛውንም ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ።**

- መስመር ላይ— ወደ PWCS.edu ይሂዱ እና በገጹ ላይኛው ቀኝ ገጽ ላይ “Auto Translate” ወይም፣ “PWCS Translations” የሚለውን ይምረጡ። በኮምፒውተር የተሰሩ ትርጉሞች ፍፁም ላይሆኑ ይችላሉ ነገር ግን ለትምህርት ቤት መረጃ ጠቃሚ ማስፈንጠሪያዎች አሏቸው። ኮምፒውተር የሌለዎት ከሆነ፣ እባክዎ የልጅዎትን ትምህርት ቤት ያግኙ።
- በአካል- የልጆን ትምህርት ቤት ወይም አንዱን አለም አቀፍ የእንኳን ደህና መጡ ማዕከል ይጎብኙ። ለ Manassas Center በ 571-402-3800 ወይም ለ Woodbridge Center በ 571-374-6813 ይደውሉ። የቋንቋውዎ ተናጋሪ በአካል የሚገኝ ካልሆነ፣ አንድ ሰራተኛ የቋንቋ ትርጉም ፖስተር፣ የቋንቋ ፍላጎቶን ለመወሰን ተጠቅሞ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይረዳዎታል።

ትምህርት ቤቶን ሲያገኙ የሚከተሉትን እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፥

- ስሞን እና የልጆን ስም፤
- የልጆን ትምህርት ቤት፣ የክፍል ደረጃ፣ እና የአስተማሪ ስም፤
- ሊያናግሩት የሚፈልጉት ግለሰብ (በስም ወይም በስራ)፣ እና የውይይቶ ርዕስ፤ እና
- ሊገኙበት የሚችሉበት የስልክ ቁጥር እና ጊዜ።

ልጅዎ ስብሰባ እንዲደረግ የሚጠይቅ መልእክት ይዞ ቤት ከመጣ፣ ወይም እርስዎ ከአስተማሪ ወይም ከሌላ የትምህርት ቤት መኮንን ጋር ውይይት ለማድረግ የሚፈልጉ ከሆነ፣ በማስተርጎም አገልግሎት ላይ ድጋፍ ለማግኘት እባክዎ ከላይ ያሉትን መንገዶች ይጠቀሙ። ቢሮዎቻችን በተቻለ ፍጥነት እርስዎን ያገኙዎታል።

የልጅዎን ስኬት ለማረጋገጥ ከእርስዎ ጋር በጋራ ለመስራት በጉጉት እጠብቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር፣

ላ ታንያ ዲ፣ ማክዴ፣ Ed.D.
የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

P.O. BOX 389, MANASSAS, VA 20108 • WWW.PWCS.EDU • 703-791-8712